ተብሎ ፡ በቍ ፡ ፲፯፻፲፱ ፡ (፫) ፡ እና ፡ ፲፯፻፳፯ ፡ የተደነገገው ፡ ሁኔታ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የመጨረሻ ፡ ውላቸው ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## (ለ) ውሎችን ፡ ለመለዋወጥ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ የፎርም ፡ ግዴታዎች ።

በባይሳ ፡ ጃሞ ፡ ከሳሽ ፤ አሰፋ ፡ ወልደ ፡ ጉጊዮርጊስ ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጽሑፍ ፡ የተፈጸመ ፡ ውልን ፡ ለመለዋወጥ ፡ ልዩ ፡ ፎርም ፡ ያስፈልጋል ፡ ወይስ ፡ አያስፈልግም ፡ በሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቶበታል ። በመጀመሪያ ፡ የቍጥር ፡ ፲፯፻፳፯ን ፡ ቋንቋ ፡ ተመልክተን ፡ ቀጥሎም ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ በተሰጡት ፡ የውል ፡ ዓይነቶች ፡ አማካይነት ፡ ትርጉሙን ፡ በመመርመር ፡ ይህን ፡ ጥያቄ ፡ እንተነትናለን ።

በፈረንሳይኛ ፡ "Les modifications au contrat originaire doivent être faites dans la forme prescrite pour ce contrat."

በአማርኛ ፡ "ዋናውን ፡ ውል ፡ የመለወጥ ፡ ጉዳይ ፡ ለዚሁ ፡ ውል ፡ በተደነገገው ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ መሠራት ፡ አለበት ።"

በእንግሊዝኛ ፡ "A contract made in a special form shall be varied in the same form."

በፈረንሳይኛው ፡ እትም ፡ ፎርም ፡ ፕሬስክሪት ፡ (forme prescrite) በሚለው ፡ ሐረግና ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ እትሞች ፡ የዚሁ ፡ ሐረግ ፡ ፍች ፡ በሆኑት ፡ ማለት ፡ በተደነገገው ፡ አጻጻፍ ፡ እና ፡ ስፔሺያል ፡ ፎርም ፡ (special form) በሚሉት ፡ ሐረጎች ፡ ላይ ፡ ሐሳባችን ፡ ሰፍሮ ፡ ማተኮር ፡ አለበት ። ጥያቄው ፡ ውሎችን ፡ ለመለዋወጥ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ፎርም ፡ እንዲፈጸም ፡ ሕጉ ፡ የሚያስገድደው ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ሁናቴዎች ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ሲሆን ፡ መልሱም ፡ ዋናውን ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ፎርም ፡ ፕሬስክሪት ፡ (forme prescrite) ወይም ፡ የተደነገገ ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ ባለበት ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የነዚህን ፡ ሐረጎች ፡ ፍች ፡ መወሰን ፡ አለብን ።

የእንግሊዝኛው ፡ እትም ፡ ይህን ፡ ሐረግ ፡ "ልዩ ፡ ፎርም" (special form) ይለዋል ። ይህ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መጥፎ ፡ አተረጓጎም ፡ ነው ። በፈረንሳይኛውና ፡ በአማርኛው ፡ እትሞች ፡ ከተሠራባቸው ፡ ሐረጎች ፡ የሚመሳሰል ፡ ትርጉም ፡ አላዘለም ። ከፈረንሳይኛው ፡ ሊፈለግ ፡ ይገባው ፡ የነበረው ፡ የተሻለ ፡ ትርጉም ፡ "አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ (በሕግ) ፡ በታዘዘ ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ የተፈጸመ ፡ ውል ፡ በዚያው ፡ ዓይነት ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ መለወጥ ፡ አለበት" ፡ በሆነ ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ በእንግሊዝኛውና ፡ በፈረንሳይኛው ፡ እትም ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ ልዩነት ፡ በእንግሊዝኛውና ፡ በአማርኛው ፡ እትም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ይበልጥ ፡ የጐላ ፡ ይሆናል ።

በተደነገገው ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ድንጋጌ ፡ ከሚለው ፡ ስም ፡ የፈለቀ ፡ ግሥ ፡ ነው ። ድንጋጌም ፡ በእንግሊዝኛ ፡ "ዲክሪ" (decree) ማለት ፡ ነው ።[7] ስለዚህ፡ የአማርኛው ፡ እትም ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ሲተረጐም ፡ "Contracts made in a legally required (or decreed) form shall be modified in the same form" ቢል ፡ ምና

7. የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ ይመለከቷል ።

ፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የውል ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ውሉን ፡ ለመለዋወጥ ፡ ልዩ ፡ ፎርም ፡ ያስፈልጋል ፤ ብሎ ፡ ማስገደድ ፡ ተገቢ ፡ የሚሆነው ፡ ስለ ፡ ውላቸው ፡ ፎርም ፡ በቅድሚያ ፡ በተስማሙት ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ራሳቸው ፡ የውላቸውን ፡ ፎርም ፡ ለመምረጥ ፡ ያላቸውን ፡ ነጻነት ፡ በዋናው ፡ ውል ፡ ፎርም ፡ ረገድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በማናቸውም ፡ የውሉ ፡ መለዋወጥ ፡ ፎርም ፡ ረገድም ፡ እንዲወሰን ፡ ፈልገዋል ፤ ለማለት ፡ የሚያስችል ፡ ምልክት ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ውል ፡ ባንድ ፡ የተለየ ፡ ፎርም ፡ እንዲፈጸም ፡ በቅድሚያ ፡ ከተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ የተዋዋዮቹን ፡ ፍላጐት ፡ አዝማሚያ ፡ ለማወቅ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ይህን ፡ መሳይ ፡ ውል ፡ ባደረጉበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ በሒሳብ ፡ መድረስ ፡ ያስፈልጋል ። ይህም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የተወሳሰበ ፡ ንግግር ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ የውል ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩን ፡ ለማመልከት ፡ ብቁ ፡ ሆነው ፡ ሊገኙ ፡ የሚችሉ ፡ የሰነድ ፡ መቀባበልን ፡ የያዙ ፡ ውይይቶች ፡ የሚፈጸሙበት ፡ ሁናቴ ፡ ነው ። ተዋዋዮቹ ፡ የተጻጻፏዋቸው ፡ ደብዳቤዎችና ፡ እነዚህ ፡ ቀደምት ፡ ውይይቶቻቸው ፡ ውል ፡ በመካከላቸው ፡ ተፈጥሯል ፤ ወደሚያሰኝ ፡ ስህተት ፡ እንዳያደርሱ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ እርግጠኞች ፡ ለመሆን ፡ ይፈልጋሉ ። ይህንንም ፡ በጽሑፍ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ውል ፡ በመካከላቸው ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ፤ በሚል ፡ በአንድ ፡ መነሻ ፡ ስምምነት ፡ ያረጋግጣሉ ።

ይህን ፡ ዓይነቱ ፡ መነሻ ፡ ስምምነት ፡ ውሉን ፡ በቃል ፡ ከመለዋወጥ ፡ እንደሚከለክል ፡ መቆጠር ፡ ይገባዋልን ? ሁልጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሊቆጠር ፡ የሚገባበትን ፡ ምክንያት ፡ ማግኘት ፡ አዳጋች ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የውላቸው ፡ መለዋወጥ ፡ በአንድ ፡ የተለየ ፡ ፎርም ፡ እንዲሆን ፡ በውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ምንጊዜም ፡ መግለጥ ፡ ይችላሉ ። ወይም ፡ ባንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ ፍላጐት ፡ የጉዳዩ ፡ አካባቢ ፡ ነገሮች ፡ ከሆኑ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴዎች ፡ ይፈልቃል ፤ ሲል ፡ በሚገባ ፡ ሊበይን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የሚያሰኝ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ውሉን ፡ ለመለዋወጥ ፡ የተደረገ ፡ የቃል ፡ ስምምነት ፡ ለመኖሩ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ከተቻለ ፡ ስለ ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ ፎርም ፡ በቅድሚያ ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ውሉንም ፡ ለመለዋወጥ ፡ ያንኑ ፡ ፎርም ፡ እንዲጠይቅ ፡ የታቀደ ፡ ነው ፤ የሚያሰኝ ፡ ምክንያት ፡ የለም ። የመነሻው ፡ ስምምነት ፡ ተግባር ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ የተፈጸመበትን ፡ ጊዜና ፡ በዋናው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ጉዳዮች ፡ ፍጹም ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። በተለይም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ የፈጀ ፡ ውይይት ፡ ሊያስነሳው ፡ የሚችለውን ፡ የሐሳብ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ለማስወገድ ፡ ይሻሉ ፡ ውይይቱ ፡ አልቆ ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ ከተፈረመ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የመነሻው ፡ ስምምነት ፡ አገልግሎት ፡ ይፈጸምና ፡ ተፈላጊነቱ ፡ ይበቃል ።

በጽሑፍ ፡ ፎርም ፡ ያለ ፡ ውል ፡ በቃል ፡ የተለወጠ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ የሚቀርብ ፡ ማስረጃ ፡ እርግጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ ሊታይ ፡ ይገባዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ማስረጃውን ፡ ፈጽሞ ፡ ላለመቀበልና ፡ ዋናው ፡ ውል ፡ የተለወጠበት ፡ የማያጠራጥር ፡ የቃል ፡ ውል ፡ ቢኖርም ፡ በቍጥር ፡ ሺ፱፻፷፪ ፡ አሳብቦ ፡ ዋጋ ፡ አይኖረውም ፤ ለማለት ፡ የሚያስችል ፡ ተገቢ ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

## መደምደሚያ ።

እነዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቊጥሮች ፡ ረቂቅ ፡ መሆናቸውን ፡ በድጋሚ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የባይሳ ፡ ጃሞ ፡ ከሳሽ ፤ አሰፋ ፡ ወልደጊዮርጊስ ፡ ተከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ ከሦስተኛው ፡ ዓይነት ፡ የውል ፡ ሁናቴ ፡ ይልቅ ፡ አራተኛውን ፡ ዓይነት ፡ የውል ፡ ሁናቴ ፡ የተመለከተ ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችልና ፡ ይህም ፡ ከሆነ ፡ ፍርዱ ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ ልብ ፡ ማለት ፡ ይጠቅማል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከሦስተኛው ፡ ዓይነት ፡ የውል ፡ ሁናቴ ፡ መመሳሰሉን ፡ ያመለክታል ፤ ይህም ፡ ከሆነ ፡ በጸሐፊው ፡ አስተያየት ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ብይን ፡ የተሳሳተ ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ።